የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.28
ADDIS ABABA 6th July, 2023

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፪/፪ሺ፲፭

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………..ገጽ ፲፬ሺ፯፻፹፮

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1292/2023

Mutual Legal Assistance In Criminal Matters Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye Ratification Proclamation ……...............Page 14,786

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፪/፪ሺ፲፭

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት እ.ኤ.አ. ሜይ ፲ ቀን ፪ሺ፳፪ በአንካራ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ባካሄደው ፲፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1292/2023

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE MUTUAL LEGAL ASSISTANCE IN CRIMINAL MATTERS TREATY BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TURKIYE</u>**

**WHEREAS,** the Mutual Legal Assistance in criminal matters Treaty between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of the Republic of Turkiye has been signed in Ankara, on the 10th day of May, 2022;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 19th regular session held on 16th day of May, 2023;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Sub-Article (1) and (12) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፪/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲ ቀን ፪ሺ፳፪ በአንካራ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>

የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Mutual Legal Assistance In Criminal Matters Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkiye Ratification Proclamation No 1292/2023".

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Treaty signed in Ankara on the 10th day of May, 2022 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of the Republic of Turkiye, is hereby ratified.

## 3. <u>Responsibility of the FDRE Ministry of Justice</u>

The FDRE Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for this implementation of the Treaty.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazetee.

**Done at Addis Ababa on this 6th Day of July, 2023.**

**SAHILEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**